## ለ"ናፍቆት ኢትዮጵያ መጽሔት" የተላከ እ-ጦማር፡-

ይድረስ፡-

ለ"ናፍቆት ኢትዮጵያ" መጽሔት አዘጋጅ፤
መልእክት ሣጥን ቍጥር ፵-፺፪-፲፬፤
ቺካጎ፣ ኢሊኖይ፤ ፷-፮፻፵።

በልዑል እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ።

የአዲሱ፡ የ፳፻፬ ዓመተ ምሕረት መግቢያ የኾነውን፡ የመስከረም ፩ ቀንን የዘመን መለወጫ በዓላችንን ምክንያት በማድረግ፡ በወጣው ቍጥር ፵፫ መጽሔትዎ ውስጥ፡ ***"እንቍጣጣሽ፣ ርዕ(እ)ሰ ዓውደ ዓመት"*** በሚል አርእስት ሥር ለሠፈረው ድርሰት ድጋፍ የሚኾኑ፡ አንዳንድ ነክ ሓተታዎች፡ "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት" ከሚለው፡ ከኹለተኛው መጽሐፌ እየተጠቃቀሱ በመታከላቸው ምክንያት፡ ስሜ ስለተወሳ፡ ያን ያዩ አንዲት ኢትዮጵያዊት እኅት፡ መጽሔቱን አምጥተው ሰጥተውኝ ተመለከትሁት።

ለድያስጶራው (በመላው ዓለም፡ በስደት ለተበተነው ኢትዮጵያዊ ወገን)፡ መልካሙን አገልግሎት የሚያበረክት ስለኾነ፡ በአጠቃላይ፡ በመጽሔቱ ዝግጅትና በያዛቸው ቍም ነገሮች፥ በሚያስተላልፉቸውም መልእክቶች፡ ያለኝን አድናቆት፡ በዚህ አጋጣሚ ልገልጥ እወድዳለሁ።

ለመግቢያ ያህል፡ ይህን ካልሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ መነሻ የኾነኝን ምክንያት ልግለጥልዎ! ይኸውም፡ ***"ዓመተ ምሕረት ወይስ? ዓመተ ፍዳ!"*** የሚል መጠይቃዊ አርእስትን የያዘው፡ የመጽሔቱ ርእሰ-አንቀጽ፡ የመልእክቱን መግቢያ፡ *"ምሕረት"* የሚለውን ቃል፡ ትክክለኛ ፍቺ በመግለጥ ከከፈተ በኋላ፥ *"ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደምድር መምጣትና ለሰው ልጅ ኃጢአት ሲል መከራን ከተቀበለ እና ያለፈውን ከሻረው በኋላ፡ ዘመኑ፡ ለምን፡ የምሕረት ዓመትነቱን አላሳየንም?"* ደግሞም፡ ወደኢትዮጵያ ኹኔታ በማምራት፡ *"ለመኾኑ፡ በአኹኑ ዘመን፡ በሕይወት ያለ ሰው፡ ካየው የደስታና የፍቅር ዘመን እና ካለፈበት ችግር ጋር ሲያነጻጽረው፡ የትኛው ጎልቶ የሚታይ ይመስላችኋል?"* በሚሉ ጥያቄዎች፡ ነገሩን በማንጠልጠል፡ *"...ከክርስቶስ ልደት ...እና ስቅለት በኋላ ያለው፡ የሰው ልጅ ታሪክ ደግሞ፡ እስካለንበት ዘመን ድረስ፡ የምሕረት ሳይኾን፡ የፍዳ ይመስላል።"* በሚሉ ኃይላተ ቃላት ተመልቶ እየተንደረደረ፡ *"እንግዴህ፡ ዓመተ ምሕረት፥ ወይም፡ ዓመተ ፍዳ መኾኑን ሳላረጋግጥ፡ እኔም፡ 'እንኳን አደረሰን!!!' ልበል መሰለኝ።"* ሲል ለደመደመው አስተያየት፡ ተገቢውን ኢትዮጵያዊ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ኾኖ ስላገኘሁት ነው።

ማብራሪያዬም፡ "በእግዚአብሔር መንግሥትነቷና በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖቷ ጸንታ፡ በነጻነት ህልውናዋ፡ ለ፯ሺ፭፻፱ ዓመታት በቀጠለችው ኢትዮጵያና በእውነተኞቹ ታማኞች ልጆቿ ዘንድ፡ ፍጥረተ ዓለሙ፡ በበኵር ልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘው የምሕረት ዘመን፡ ቀድሞ እንደነበረው፡ ዛሬም፥ ለወደፊቱም፡ ለዘለዓለሙ፡ እውንና የተረጋገጠ ሕይወታቸው ኾኖ፡ "የምሥራች! እንኳን አደረሰን!" እየተባባሉ የኖሩበትና የሚኖሩበት መኾኑ ጭምር ይታወቅ እንጂ!" በሚል አጭር የአንክሮ ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል።

አዎን! ጥፋትንና ክፋትን፥ ኃጢአትንና ፍዳን፥ መርገምንና ሞትን፡ ቀድሞም፡ ከመጀመሪያው፡ በፈጣሪው መልክ በመፈጠሩና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ለመባል በመብቃቱ፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ ከራሱ የጠነሰሰው፥ ከዚያ በኋላም፥ እስከዛሬ ቀጥሎበት፡ በመጨረሻ፡ በራሱ ምርጫ፥ በራሱ ላይ፡ እኒህን ኹሉ ጠንቆች ያመጣው፡ ራሱ፡ ሰው መኾኑም ይታወቅ እንጂ! ይህማ፡ እንዴት ሊዘነጋ ይገባል? አይገባም። ይህም፡ በአብዛኛዎቹ የዓለም ሃይማኖቶች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ እውነታ ኾኗል።

እግዚአብሔር፡ እነዚህን፡ አሉታውያን ባሕርያት እኮ አልፈጠረም። እርሱ፡ በራሱ መልክና ባሕርይ አልቆና አክብሮ ለሠራው፡ ለፍጡሩ ፍጹም በጎ ህልውና፡ ጥንቱኑ የፈጠረለትስ፡ ልማትንና መልካምን፥ ጸጋንና ምልዓትን፥ በረከትንና ሕይወትን ነው፤ ፍጡሩ ሰው ግን፡ የፈጣሪውን ሥርዓት መከተልን፡ "አልፈልግም!" ብሎ፡ በራሱ የዕብሪትና የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት እውቀቱና ፍላጎቱ ያደረገው ምርጫ፡ የእነዚያ፡ እርሱ የፈጠራቸው፡ ፀረ-እግዚአብሔር የኾኑት ድርጊቶቹ፡ ሰለባ ኾኖ፥ ለእነርሱም ተዳርጎ፡ ቀድሞም፥ ዛሬም፡ ይኸው እስካኹኗ አፍታ ድረስ፡ በግለሰብና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በአገረሰብ፣ በዓለም-ዐቀፍና በፍጥረተ-ዓለም ደረጃ፡ በመከራና በሥቃይ ሲማቅቅ ይገኛል።

ከዚህ ውስብስብና ውጥንቅጥ መቅሠፍታዊና ጽልመታዊ ፍዳ ወጥቶ፡ ፈጣሪው፡ ከጥንት ያዘጋጀለትን የክብርና የብቅዓት ኑሮ መልሶ የማግኘት ዕድሉን፡ በመለኮታዊው የትስብእት ቤዛነቱ አበርክቶለት እያለም እንኳ፡ ከዚህ የጕሥቍልና አካኼዱ ተጸጽቶ፡ (በንስሓ) ሊመለስ አኹንም አልፈለገም፤ አልመረጠምም።

እንዲያውም፡ ይባስ ብሎ፡ በኢትዮጵያም ኾነ፡ በውጭው ዓለም የሚኖረው፡ የሰው ልጅ፡ (ሳያፍር፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን፡ የዛሬውን ትውልድ ጨምሮ)፡ በግለሰብና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በአገረሰብ፣ በዓለም-ዐቀፍና በፍጥረተ-ዓለም ደረጃ፡ እንደገና፡ በራሱ የዕብሪትና የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት እውቀቱና ፍላጎቱ ባደረገው ምርጫ፡ "እምቢ! አሻፈረኝ!" ብሎ፡ በዘመነ ምሕረት ከመኖር ይልቅ፡ አኹንም፡ በዘመነ ፍዳ መማቀቅን የመረጠው፡ ያው፡ ራሱ፡ ሰው እኮ ነው!

በርእሰ አንቀጽዎ፡ *"ይኽንን፡ በዚህች አጭር የመልእክት ገጽ ላይ፡ መጀመር እንጂ መጨረስ ስለማንችል"* ሲሉ እንደገለጹት፡ ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት፡ እዚህ ላይ፡ ማተቱን ገትቼ፡ በዚህ ረገድ፡ በምልዓት የተዘጋጀው ሓተታዊ ማብራሪያዬ፡ ዝርዝራቸው፡ www.ethkogserv.org የሚል አድራሻ ባለው ጎዋ ሰሌዳችን ላይ ተመልክቶ በሚገኙት መጻሕፍቴ፥ በተለይ ግን፡ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዤ

በላክኋቸው፥ ባለፈው ፳፻፫ ዓ. ም. በተላለፉ ሦስት መልእክታት ውስጥ፡ በስፋት ተተችቶበትና ተካትቶ ስለሚነበብ፡ እነዚህኑ ጽሑፎች፡ በበኩልዎ ተመልክተዋቸው፥ ለመጽሔትዎ አንባቢዎች እንዲደርሳቸው ቢያደርጉ፡ ከዚሁ ምንባባቸው፡ የመንፈስ ቅዱስን እውቀትና መጽናናትን ሊያተርፉ እንደሚችሉ በማመን፡ ማሳሰቢያዬን፡ በዚሁ እፈጽማለሁ።

እዚህ ላይ፡ እግረ መንገዴን፡ ላስታውስዎ የምሻው፡ ሌላ ቍም-ነገር አለ፤ ይኸውም፡ የሥነ ፊደላችንን ሥርዓት አጠባበቅ የሚመለከተው ነው፤ በዚህ ረገድ፡ በመጽሔቱ ውስጥ የተደረገውን የጥንቃቄ መጠን፡ ከአንዳንዶች ሌሎች መሰሎች ጋር ሳመዛዝነው፡ የተሻለ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፤ ይኹን እንጂ፡ በአጻጻፍ ወይም፡ በኅትመት ጕድለት ይኹን፥ አይኹን አላውቅም፡ አልፎ አልፎ፡ አንዳንድ ግድፈቶችን ስላየሁ፡ ይህን የመሰለው ስሕተት፡ በተለይ በአንድ መጽሔታዊ ርእሰ-አንቀጽ ውስጥ ተፈጽሞ አይቶ ማለፍ አግባብ ስላልኾነ፡ ያን ለማስታወስ ስል፡ ይህን ማሳሰቢያ መጨመር አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

ለምሳሌ፡ እርእሰ-አንቀጹ መግቢያ ላይ ካሉት መካከል፡ ጥቂቶቹን ብቻ ለመጠቈም ያህል፡ ሊጻፍበት የሚገባው ሆሄ እየተተወ፡ "ስሕተት" የሚለው፡ "ስሁተት"፤ "ኾኖብኝ" የሚለው፡ "ሆኖብኝ"፤ "ለተነሣሁበት" የሚለው፡ "ለተነሳሁበት"፤ "ኹለት" የሚለው፡ "ሁለት"፤ መጽሐፍ" የሚለው፡ "መፅሐፍ"፤ "ከሰማየ ሰማያት" የሚለው፡ "ከሠማየ ሠማያት"፤ "ማርያም" የሚለው፡ "ማሪያም"፤ "ኀጢአት አንጽቶ ...ሊያድነው" የሚለው፡ "ኀጢያት አንፅቶ ሊድነው"፤ "ለሰው ልጅ" የሚለው፡ "ለሠው ልጅ"፤ "ሃይማኖት" የሚለው፡ "ኃይማኖት"፤ "ንጹሑን" የሚለው "ንፁሑን"፤ "የንጹሐን" የሚለው፡ የንፁሃን"፤ "በሰላም" የሚለው፡ "በሠላም" ተብሎ ተጽፏል።

በመንፈስ ቅዱስ ጸጋውና በረከቱ ያልተለየንን፡ የቸሩ ፈጣሪያችንንና የቅድስት እናቱን ፈቃድ ለመፈጸም፡ እየራሳችንን እንድናበቃ በማሳሰብ፡ በዓለ ብሥራተ ትስብእቱን እንዳከበርን ኹሉ፡ ከበዓለ አስተርእዮውና ጥምቀቱ ደግሞ ደርሰን፡ በእውነተኛው አምልኳችን፡ "የምሥራች! እንኳን አደረሰን!" ለመባባል ያብቃን!

ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥቷ ኢትዮጵያ አገልጋይ።

---